# "... አንድ ኮማንዶ..."

### ሀ

**የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)**

1. የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ሕብረት
2. የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ዲሞክራት
3. ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር፣
4. ትንሳኤ የኢትዮጵያ አረበኞች ሕብረት
5. ታጠቅ ለነጻይቱ ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ
6. የኢትዮጵያ መድህን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ
7. የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በካናዳ
8. የኢትዮጵያ የሲቪክ ማሕበረት ስብስብ በእንግሊዝ አገር
9. የኢትዮ-ካናዳ የዲሞክራሲ መድረክ
10. የኢትዮጵያብሔራዊ ሽግግር ኮውንሰል
11. የኢትዮጵያውያን የጋራ መድረክ በኖርዌይ
12. የዳላስ ሁሉን አቀፍ ጉባዔ ድጋፍ

### ለ

**‹‹የኢትዮጵያ የፖለቲካና የሲቪክ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች የጋራ መርሆና የትግል ጥሪ››**

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)
2. ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነት ለፍትህ በኢትዮጵያ
3. የኢትዮጵያ አበይት ጉዳዮች መወያያ ሒደት፣
4. ብሩህ ኢትዮጵያ ሕዝባዊ ንቅናቄ
5. ኦነግ (በጄኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው)
6. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሽግግር ምክር ቤት
7. ዓለም አቀፍ ሕዝባዊ ንቅናቄ ለለ ውጥ በኢትዮጵያ/በቃ፣
8. መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ(መ.ኢ.ሶ.ን.)
9. የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
10. Advocacy for Ethiopia
11. March 4 Freedom.

### ሐ

**‹‹የሕዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዴሞክራሲ››**

1. ኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)-ኢብሳ
2. ኦጋዴን ብሔራዊ ነጻነት ግንባር፣
3. የሲዳማ ነጻነት ግንባር
4. ሌሎች እጩ አባል ድርጅቶች

### መ

**‹‹የኢትዮጵያውያን ጥምረት ለዲሞክራሲያዊ ለውጥ››**

1. የጋምቤላ ሕዝብ ነፃነት ንቅናቄ
2. የቤኒሻንጉል ሕዝብ ንቅናቄ
3. የኢትዮጵያ ሕዝቦች ፍትህና እኩልነት ግንባር
4. የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር
5. የአማራው ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ
6. የትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ

---

አንባቢዎች ከላይ ቀድመው የተቀመጡትን ሰንጠረዦች ልብ ብላችሁ ተመልከቷቸው። ከዚህ በታች የሚሰፍረው ቃል ስለነሱ እየተረከ ይሄዳል ተከታተሉ፣

መሰባሰብ መልካም ነው። የመሰባሰብ ዘመን ውስጥም እንገኛለን። ስለሆነም ነው እኔም ስብስቦቹን ሰብስቤ በቅድሚያ ያሰቀመጥኳቸው። ትንሽ ትንሽም ቢሆን በየመደባቸው የምልላቸውም አለኝ፣- ከሰንጠረዥ ‹‹ሀ›› ልጀምር፣ ከ18 - 20 ሜይ 2012 በኦታዋ ካናዳ የተጠራው ጉባዔ ‹‹...ለአንድነት የግንባር ምሥረታ...›› የሚል ሲሆን፣ ጉባኤው መስርቶ የተነሳው ግን፣ ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ሸንጎ (ሸንጎ)›› የሚል ነው። ለምን ግንባር ምሥረታው ቀርቶ ወደ ሸንጎ እንደተቀየረ የሚገልጽ ምንም ዓይነት መግለጫ አልሰማሁም። ይህን ጉባዔ ለማዘጋጀት ከሁለት ዓመት ተኩል በላይ ውጣ ውረድን እንደጠየቀ፣ አዘጋጆቹ በተደጋጋሚ በተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች ሲገልጹ እንደነበረ ይታወሳል። ሸንጎው በሰንጠረዡ ከ1 እስከ 6 ተራ ቁጥር የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ከ7 እስከ 12 የሲቪክ ማህበራት የሚላቸውን ያቀፈ ሲሆን፣ በድምሩ 12 ስብስቦችን አካቷል። ይህ ሸንጎ ከተቋቋመበት ጊዜ በኋላ ያሉት ወራቶች የተለያዩ ድርጅቶች በአንድ ወይም በሌላ ስም የሆነ ትብብር መፍጠር የጀመሩበት ዘመን ነበር ማለት ይቻላል። ወደ ሰንጠረዥ ‹‹ለ›› ተሻገሩ፣ ‹‹የኢትዮጵያ የፖለቲካና የሲቪክ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች የጋራ መርሆና የትግል ጥሪ›› የሚባለው በሰንጠረዡ የ12 ድርጅቶች ስብስብ የሆነውን ሸንጎንና ሌላ አንድ ጥምረትንና 9 ነጠላ ድርጅቶችን ጨምሮ በድምሩ 11 ስብስቦችን አካትቶ ነሃሴ 1ቀን 2004 ዓ.ም. ተቋቋመ። ይህ የሆነው ሸንጎ ከተቋቋመ ከሁለት ወር ተኩል ባነሰ የጊዜ ርቀት ውስጥ ነው። የትና መቼ ተሰብስቦ እንደተፈጠረ የሚታወቅ ነገር የለም። እንደሸንጎው በዓመትና በወራት የሚቆጠር ውጣ ውረድ እንዳልነበረበት ግን ግልጽ ነው። የተቋቋመበትን ጊዜ በተመለከተ ግን የግድ እሳቤ ውስጥ መግባት ያለበት ጉዳይ አለ።

ጊዜው የጠቅላይ ሚኒስትር መለሰ ዜናዊ ሕመማቸውና ሞታቸው በፈረቃ ተቃዋሚንም ሆነ ደጋፊን ዥዋዥዌ ሲያጫውቱት የነበረ ጊዜ ሲሆን፣ በተቃዋሚ በኩል መለስ ሲሞቱ ቢሯቸው ክፍት ስለሚሆን፣ ስልጣን የሚጠብቃት እረኛ በማጣቷ፣ ከቤተመንግሥስት ወጥታ ስትበር በወጥመድ ለመያዝ ያሰፈሰፈ ይመስል ነበር ቢባል፣ ብዙ የሚያሳማ ግንዛቤ አይመስለኝም። በዚያው ሰሞንም ነበር ጥምረትና ኦነገ (የጄ/ል ከማል ገልቹም) አሊያንስ ፈጠሩ ተብሎ የተወራው፣ ነገር ግን ወሬውን አጣጥመን ሳንጨርስ፣ በነሃሴ 1ቀን 2004 ዓ.ም. የተቋቋመው ስብስብ (ሰንጠረዥ ‹‹ለ››) ውስጥ ሁለቱ የአሊያንስ አባል ድርጅቶች ተነጣጥለው ገብተው እናገኛቸዋለን፣ ከዚያ ወዲህም የአሊያንስ ጉዳይ ኮሽታው ይጠፋል። ከዚህ ወደ ሰንጠረዥ ‹‹ሐ›› ፊታችንን ስናዞረ ደግሞ፣ ጁላይ 25ቀን 2012 ‹‹የሕዝቦች ትብብር ለነጻነትና ለዴሞክራሲ›› በሚል በሰንጠረዡ ከ1 እስከ 3 ተራ ቁጥር ያሉትን ስብስቦችና ሌሎች ስማቸውና፣ ቁጥራቸው ወዘተ የማይታወቅ በ4ኛ ተራ ቁጥር ላይ እጩዎች የሚላቸውን አቅፎ መቋቋሙን እናጤናለን። በነገራችን ላይ እኔ ይህቺን በምጫጭርበት ሰዓት ከነዚህ 4 ስብስቦች ውስጥ በተራ ቁጥር 2 የተቀመጠው የኦጋዴን ንቅናቄ ከወያኔ/ኢሕአዴግ ጋር ድርድር ተቀምጧልን እየሰማን ነው። ትንሽ ለየት ያለ የምስራች የሚባል አንድ የማስታውሰው ደግሞ፣- ግንቦት 7ትን፣ የአፋር ፓርቲን፣ የኢትዮጵያ አንድነትና ፍትህ ንቅናቄን አቅፎ ከተቋቋመው ጥምረት በሚል ከሚታወቀው ስብስብ ውስጥ ሁለቱ፣ ማለትም የኢትዮጵያ አንድነትና ፍትህ ንቅናቄና ግንቦት 7 መዋሃድ ነው። ውህዱ ግን ማን እንደሚባል መረጃ የለኝም። ያም ሆነ ይህ ግን፣ የዛሬው ጥምረት የሁለት ድርጅቶች ጥምር - የአፋር ፓርቲና ውሕዱ ነው ማለት ነው። አሁን ሰንጠረዥ ‹‹ሐ›› ላይ ደርሰናል፣ በዚህ ሰንጠረዥ ውስጥ የተዘረዘሩት

ድርጅቶች ደግሞ፣ ‹‹የኢትዮጵያውያን ጥምረት ለዲሞክራሲያዊ ለውጥ›› የሚለውን መስከረም 17 2005 ያቋቋሙት ሲሆን፣ ይሄኛውን ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው አንድ ነገር አለ። የቀደሙቱ በሙሉ መናኸሪያቸው አውሮፓና አሜሪካ ሲሆን፣ እነዚህኞቹ ግን የከተሙት በአንድ የጎረቤት አገር ውስጥ ነው።

ሌላው መጤን ያለበት ደግሞ፣ እነዚህ ስብስቦች የተፈጠሩት ከሜይ 20ቀን 2012 እስከ መስከረም 17ቀን 2012 ድረስ ከአምስት ወር ባልበለጠ የጊዜ ርቀት ውስጥ ሲሆን፣ ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸው ጉዳይ ደግሞ፣ እስካሁን ከአንዳቸውም ቢሆን ይህ ተፈጸመ፣ ያ ተደረገ፣ እዚህ ደረስን፣ እዚያ ጀምረናል የሚል ነገር የለም። ሰንጠረዥ ‹‹ሐ›› እና ‹‹መ›› ን በተመለከተ ለግንዛቤያችሁ እንዲሆን ከማድረግ ያለፈ የምገፋበት ሃሳብ የለኝም። ስለ ሰንጠረዥ ‹‹ሀ›› እና ‹‹ለ››  ግን የሚከተለው አለኝ።

ሁለቱን ሰንጠረዦች ልብ በሏቸው። ሸንጎውን ያቋቋሙት ተዋንያን ደጋግመው እንደነገሩን፣ በሁለት ዓመቱ የዝግጅት ጊዜ ካጠፉበት አንዱና ዋናው ጉዳይ፣ አሉ የተባሉ የፖለቲካና ሌሎች ስብስቦችን በመቅረብና በማወያየት ዛሬ ሸንጎ ይዞት ለወጣው መፈክር ተባባሪዎችን ለማሰባሰብ ያደረገው ጥረት አንደነበረ ነው። አባባሉን እንያዘውና ታዲያ፣ ሸንጎው በሜይ ወር በተቋቋመበት ጊዜ በሰንጠረዥ ‹‹ለ›› ውስጥ ከቁጥር 2 እስከ 11 ድረስ ካሉት ስንቶቹ ናቸው የሸንጎው አዘጋጅ ሊደርሳቸው ያልቻለው? ወይስ ደርሷቸው አልተቀበሉትም? ወይስ ስብስቦቹ ሸንጎው ከተቋቋመ በኋላ የተፈጠሩ ናቸው? ወይስ ጭራሹኑ ድርጅቶቹን ሸንጎው ሊያሰባሰባቸው አልፈለገም? መልስ የለኝም። ከጥያቄዎቹ ጋር ልተዋችሁ።

ስለነዚህ በየመልኩ የዘረዘርኳቸው ስብስቦች መረሳት የሌለበት ጉዳይ ግን፣ የሁሉም ዋና አላማ የወያኔ/ኢሕአዴግን ሥርዓት የሚቃወሙ፣ ሊያስወገዱትም የሚሹና የማስወገጃውንም ዘዴና መላም ይጠቋቁሙ መሆናቸው ነው። በተጨባጭ እየሆነ ስላለው ጉዳይ ግን ቀደም ብዬ እንደጠቆምኩት በይደር ከምይዘው በስተቀር መልስ የለኝም። ከዚህ ቀጥሎ ግን፣ ጉዳዩን ከተነሳሁበት ርዕስ ‹‹…አንድ ኮማንዶ…›› ከሚለው ጋር ያለውን ግንኙነት ላመላክትና ሃሳቤን ልቋጭ፡፡

ነገሩ እንዲህ ነው። በደርግ ዘመን የነበሩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክረስቲያን ፓትርያሪክ አቡነ ቴዎፍሎሰ በጸረ-አብዮትነት ታስረው በነበረበት ጊዜ ከመገደላቸው በፊት፣ አብረዋቸው ታስረው ከነበሩ አንድ ሰው ጋር ሲጨዋወቱ - ልክ እኔ ዛሬ ለእናንተ እነዚህና እነዚያ ድርጅቶች፣ ስብስቦች… ወዘት እያልኩ ከላይ እንደደረደርኩላችሁ - ሰውየውም ስለቤተሰቡ እንስቶ ሲያወራላቸው፣ በርከት ያሉ የኮማንደርነት ማዕረግ ያላቸው ዘመዶች እንዳሉት በመዘርዘር እከሌ የተባለው አጎቴ ኮማንደር ነው። እከሌ የተባለ ወንድሜም ኮማንደር ነው። እከሌ የተባለው ያጎቴ ልጅ ኮማንደር ነው እያለ ሲደረድርላቸው በሚገባ ካዳመጡት በኋላ፣ ለነገሩ ደህና ደህና ዘመዶች ናቸው ያሉህ፣ ግን እኮ ታዲያ ከዚህ ሁሉ ኮማንደር ይልቅ አሁን የሚያስፈልገው አንድ ኮማንዶ ነበር አሉት ይባላል። አንባቢዎች እንግዲህ የኔን ድርድሮች በደንብ ካጤናችሁ በኋላ ከዚህ ሁሉ እኮ ታዲያ … ብላችሁ ቀጥሉበት።
መልካም ጊዜ፡፡

አሸብር ነኝ
ashebir@t-online.de